# ፅናት

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት) ልሳን






ቅጽ 1 ቁጥር 3 | ቅዳሜ የካቲት 27 2002 ዓ.ም | ዋጋ 2 ብር




ኢትዮጵያዊቷ የዴሞክራሲ፣ የፍትህና የነፃነት ታጋይ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ 420 ቀናትን በእስር ላይ ትገኛለች . . . የአ.አ ነዋሪዎች በመድረክ ስብሰባ ላይ በአስቸኳይ እንድትፈታ ጠየቁ:: መንግሥትም እሷን በመፍታትዴሞክራትነቱን በተናባር ማረጋገጥ አለበት ብለዋል::

## በውስጥ ገጾቻችን


⇒ የኢህአዴግ ነጠላ ዜማ. . .ገጽ 2

⇒ ኢትዮጵያ ያለ ወደብ. . .ገጽ 3

⇒ ያለ ሠላም እድገት. . .ገጽ 5

⇒ የዴሞክራሲ ጥብቆ . . .ገጽ 6


# መድረክ ከአዲስ አበባ ነዋሪዎች ጋር መወያየት ጀመረ



የስምንት ፓርቲዎች ጥምረት የሆነው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ (መድረክ) ቅዳሜ የካቲት 14 ቀን 2002 ዓ.ም በወረዳ 10 ጉለሌ ክፍለ ከተማ ድልበር ት/ቤት አዳራሽ ከአዲስ አበባ ነዋሪዎች ጋር ውይይት አካሄደ:: እነዲሁም በሳምንቱ የካቲት 20 ቀን 2002 ዓ.ም የመርካቶና አካባቢው ነዋሪዎችን በአዲስ ከተማ ት/ቤት አዳራህ ውይይት አካሂዷል:: በአዲስ አበባ የሚወዳደሩ እጩዎችንም አስተዋውቋል::

በድልበር ት/ቤት በተካሄደው ሕዝባዊ ውይይት ላይ በርካታ ታዳሚ ዎች የተገኙ ቢሆንም በርካታ የከተማው ነዋሪዎች ጥሪውን እንዳልሰሙ ለማወቅ ተችሏል:: በአዲስ ከተማ ት/ቤት ግን አዳራሹ ከመሙላትም አልፎ መጨናነቅ ተፈጥሮ እንደነበር የፅናት ጋዜጣ ዘጋቢ ተመልክቷል:: ሕዝቡ በንቃት በመሳተፍ ለመድረኩ አመራር አካላት የተለያዩ ጥያቄዎችን በማቅረብ

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የመድረክ የአርባጉጉ ተጠሪና እጩ ተወዳዳሪ ከፍተኛ ድብደባ ደረሰበት



እጩ ተወዳዳሪ አበበ ቦጋለ ቱለማ በአርሲ ዞን የአርባጉጉ የመድረክ ተጠሪ ነው:: የደረሰበተን ድብደባና በተለያዩ ጊዜያት የሚደርሱበትን ጫናዎችና ዛቻዎች ለአንድነት ፓርቲ በጻፈው ሪፖርት አስታውቋል::

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የመድረክ እጩ ተወዳዳሪ በምርጫ ቦርድ ታገዱ

አቶ አዕምሮ በአንድነት ፓርቲ ውስጥ የብ/ም/ቤት አባልና የሰሜን ቀጠና ኮሚቴ አስተባባሪ ናቸው:: በ2002 ምርጫ ለተወካዮች ም/ቤት መድረክን በመወከል ለመወዳደር በምስራቅ ጐጃም ዞን አማኑኤል ወረዳ ተመዝግበው ምርጫ ቦርድ ያወጣውን የአጩነት መስፈርት አሟልተው እስከ ፩ኛው ቅፅ ድረስ በመሙላት የእጩነት መታወቂያ እንደተሰጣቸው ይናገራሉ:: ነገር ግን ባላወቁትና ግልፅ ባልሆነላቸው ምክንያት ስልክ ተደውሎ የአካባቢው ተወላጅ ስላልሆንክ

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ የመድረኩ ሊቀመንበር ሆኑ

ከመድረክ ጠቅላላ ጉባዔ 56 ተወካዮች ውስጥ ከ43 ሰው በላይ በተሳተፈበት የመድረክ በሁለተኛ ጠቅላላ ጉባዔ ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ ሊቀመንበር እንዲሁም አቶ ገብሩ አስራት ተቀዳሚ ም/ሊቀመንበርና የምርጫ ጉዳይ ኃላፊ ሆነው ለቀጣዩ አራት ወራት እንዲሰሩ ተመርጠዋል:: የካቲት 20 ቀን 2002 ዓ.ም በተካሄደው ጠቅላላ ጉባዔ ላይ የተነሱ አጀንዳዎች (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የዓረና እጩ ተወዳዳሪ በጩቤ ተወግተው ተገደሉ

የዓረና ትግራይ ለዴሞክራሲና ለሉአላዊነት በትግራይ የተወካዮች ምክር ቤ ት ተወዳዳሪ አቶ አረጋዊ ገብረ ዮሐንስ በጩቤ ተወግተው መገደላቸው ተረጋገጠ:: የካቲት 22 ቀን 2002 በመቀሌ ከተማ ከሌሊቱ በ9 ሰዓት አቶ አረጋዊን የገደሉት ሰዎች ከሟች ጋር ምንም አይነት ግንኙነት እንዳልነበራቸውና ግድያው ፖለቲካዊ ተልዕኮ እንደነበረው የዓረና ትግራይ ሊቀመንበር አቶ ገብሩ አሥራት ገልጽዋል::

ቀደም ብሎም ለንግድ ሥራ በዛላ አንበሳና በሌሎች ቦታዎች ሲንቀሳቀሱ በተ ደጋጋሚ እየታሠሩ ከገኘው ፖርቲ አባላት ማስፈራሪያ ይሰነዘርባቸው እንደነበር ለፖርቲው ጽ/ቤት ያስታወቁ እንደነበር

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

# ምርጫችሁ በእጃችሁ ነው!!

# መልዕክተ ፀናት

## የኢህአዴግ

## «ተቃዋሚዎች አገር መምራት አይችሉም»

## ደካማ ነጠላ ዜማ

በቅርቡ በተሌቭዥን በተደረጉ ፖለቲካዊ ክርክሮች ኢህአዴግ «ተቃዋሚዎች አገርን መምራት አይችሉም።» የሚል የማጣጣያ ነጠላ ዜማ በተደጋጋሚ አሰምቷል። ደካማ፣ጠባብና የተሳሳተ ዜማ ነው። ለአባባሉ ከሚሰጣቸው ምክንያቶች ዋናዎቹ «እርስበርሳቸው አይስማሙም፣ በውስጣቸው ዴሞክራሲ የለም፣ሃገራዊ ራዕይ የላቸውም» የሚሉ ናቸው። እነዚህ ምክንያቶች በጥቃቅንና ወቅታዊ ክስተቶች ላይ የተመሠረቱና የተቃዋሚዎችን መሠረታዊ ባህሪ የማይገልፁ ናቸው።

አገር መምራት ማለት ምን ማለት ነው? አገር መምራት ማለት በቅድሚያ ራዕይ ማስቀመጥ ማለት ነው አንድ አገር ሊከተለው የሚገባው አቅጣጫ የሚደርስበትን ግብ ማሳየት ማለት ነው። ከዚያ በመቀጠል የራዕይ ማስፈጽሚያ ስልቶችን መቀየስና ነፃነትን በተጎናጸፈ፣የጉዳዩ ባለቤት የሆነውን ሕዝብ በንቃት ባሳተፈ በአስተሳሰብና ከሙስና በፀዳ መንገድ ተግባራዊ ማድረግ ማለት ነው።

አሁን እያተኮርን ያለው ስለአመራርና ስለመሪ ኃይል ነው። መዘንጋት የሌለበት በብዙ መቶ ሺዎች የሚቆጠር ከፍተኛ ዕውቀትና ልምድ ያለው የመንግሥት ሠራተኛ መኖሩ ነው። ይህ በምርጫ አሸንፎ በሥልጣ ላይ የወጣ ፖርቲ አመራርን ይጠብቃል። ይህ ኃይል ጥሩ አመራር ካገኘና የመፍጠር ችሎታውን እየተጠቀመ በነፃነት እንዲሠራ ከተደረገ ተዓምር የሚሠራ ኃይል ነው። ይህ ኃይል ሰብአዊና ዴሞክራሳያዊ መብቶቹ የሚከበሩለት መሆኑን ከአወቀ የመሪው ፖርቲ የጀርባ አጥንት ነው።

ስለአንድ አገር መሪ ኃይል ሲወሳ መነሳት ያለበት መሠረታዊ ጥያቄ የኢትዮጱያ ሕዝብ እንደ ሕዝብ ይህችን አገር ከድህነት አላቅቆት ነፃነት በሰፈነበት የልማት ጐዳና ሊመራት የሚችል የተማረና ብቃት ያለው የሰው ኃይል አላት ወይስ የላትም የሚል ነው። መልሱ አላት እንጂ በሚገባ! የሚል ነው። በአሁኑ ጊዜ የተማረና ብቃት ያለው አመራር ሊሰጥ የሚችል የሰው ኃይል እንኳን ለኢትዮጱያ ለአፍሪካ፣ለአሜሪካ፣ለአወሮፖና ለሌላው ክፍለ ዓለም ይተርፋል ተርፏልም። የአንድ በሥልጣን ላይ የወጣ ፖርቲ ዋና ሥራ ይህን የሙያተኛ ኃይል ለይቶ ማወቅና ከወስጡ መርጦ ለሃገር ሥራ አመራር ላይ ማስሰለፍ ነው።

መድረክ በምርጫ አሸንፎ ሥልጣን ቢይዝ የአመራር ኃይል አንጥሮ የሚያወጣቸው ምንጮች አራት ናቸው። አንደኛው ምንጭ መድረክ ራሱ ነው። የስምንት ፖርቲዎች ስብሰብ የሆነው መድረክ በውስጡ በተለያየ ሙያ የሠለጠኑ፣በትግል የተፈተኑ፣ሃገራዊ ራዕይ ያላቸውና ራዕያቸውን እውን ለማድረግ የተዘጋጁ ወጣቶችና አዛውንት አሉት። ከእነዚህ መርጦ በአመራር ቦታዎች ላይ ያስቀምጣል።

ሁለተኛው ምንጭ የመድረክ አባላት ያልሆኑ ነገር ግን ራዕዩን የሚደግፉ የጠለቀ የሙያ ዕውቀትና የዳበረ ልምድ ይዘው በሃገር ውስጥ በተለያዩ የጥናትና ምርምር ተቋማትንና ሌሎች አገር በቀልና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ውስጥ የሚሠሩ ሙያተኞች ናቸው።

ሶስተኛው ምንጭ የኢህአዲግ ካምኘ ነው። መድረክ ለአገር የሚጠቅም ሙያና ልምድ ያላቸው ችሎታቸውን በተግባር ያስመሰከሩ ሕዝብን ያልበደሉ ሰዎች ካሉ እነሱን ለመፈለግ ኢህአዴግ ካምኘ ውስጥ ከመግባት ወደኋላ አይልም።

አራተኛው ምንጭ በውጭ አገር የሚኖሩ አትዮጱያውያንና ትውልደ ኢትዮጱያውያን በዓለም ላይ ተሰራጭተው ይገኛሉ። ከእነዚህ ውስጥ በሙያቸው አንቱ ተብለው በከፍተኛ የኃላፊነት ቦታ ላይ የሚገኙ በርካታ ናቸው። መድረክ እነዚህን በመብራት ፈልጐና አግኝቶ እውቀታቸውንና ልምዳቸውን ለሃገራቸው እንዲያውሉ «የእናት አገር ጥሪ» ያደርጋል።

መድረክ ከዚህ በላይ በተጠቀሱት አራት መንገዶች መረቡን አስፍቶ በመዘርጋት መሪዎችን ያሰባስባል። ከዚህ አኳያ ኢህአዴግ ተቃዋሚዎች «አገር መምራት አይችሉም» ሲል ከእኔ ውጭ ኢትዮጱያን ለመምራት የሚችል ኃይል ማሰባሰብ አይችሉም ማለቱ ነው። ይህ ግን በጠባብ እይታ ላይ የተመሠረተ የተሳሳተ አመለካከትና ደካማ አስተሳሰብ ነው።

# ደብዳቤዎቻችሁ

## መድረኮች

በሚገባ ሕዝብ ልብ ውስጥ አልገባችሁም ስለዚህ በቀረችው ጊዜ ልደቱ ከሕዝብ ልብ እንደወጣ እናንተ ደግሞ ወደ ሕዝብ ልብ ዘልቃችሁ መግባት አለባችሁ።

ይሄንን አምባገነን ስርአት የፈለገውን ቢሠራ ርቃኑን ቀርቷል። ስርዓቱ በብዙ ችግሮች የተተበተበ ሰለሆነ 5 ደቂቃ የተሌቭዥን ክርክር ብቻ በቂ ይመስለኛል የእኔ ጥያቄ ይህ ስርዓት ከተሸነፈ በኋላ ስልጣኑን ይለቃል ብላችሁ ታስባላችሁ?

**O= ORGINAL LEADER**

**R= REVOLUTION**

**A= AGAINST 4**

**N= NATIONALITY**

**G=GROUP IN**

**E= ETIOPIA**

ከደሴ የስልክ መልዕክት ነው

## የአርባ ጉጉ ተጠሪ . . .

ከገጽ 1 የዞረ

በሪፖርቱ ላይ እንደተገለፀው ከሆነ በ19/6/2002 ከቀኑ 8:00 ሰዓት ሲሆን የመድረክ ተጠሪ እንደመሆኑ መጠን እጩ ተወዳዳሪዎችን ለማስመዝገብ ከሚኖርበት ከርኤ ከተማ ወደ አቦምሣ ከተማ በመሄድ ላይ እንዳለ ከኋላው አንድ የመንግሥት መኪና ድንገት በመድረስ አብረውት ከሚሄዱት ሰዎች መሀከል እሱን ጠርተው «አንተ እጩ ተወዳዳሪ ስለሆንክ እንተባበርሃለን ግባ» ብለው መኪና ውስጥ ካስገቡት በኋላ አቦምሳ ይዘውት እንደ ሄዱ አበበ ቦጋለ ይናገራል። አያይዞም አቦምሣ ከተማ እንደደረሱ ከመኪና ሲወርድ ሁለት ሰ ዎች ፊታቸውን በጨርቅ የተሸፈኑና ደረጃ ጥላ የተባለው የኢሕአዴግ አባል በፌሮ ብረት ከፍተኛ ድብደባና የመግደል ሙከራ እንዳደረሱበት በምሬት በሪፖርቱ ላይ ገልጿል።

አበበ ቦጋለ በመቀጠልም ከጭንቅላቱ ላይ በደረሰበት ድብደባ ወድቆ እንዳለ ሻንጣውንና ከሻንጣው ውስጥ ያለውን 1275.25 ብርና ሌሎች ዕቃዎችን 2 ሞባይሎችና ከሁለት ካርዶች ጋር ወስደውብኛል ይላል። ደሙን እያፈሰሰ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ሄዶ አቤት ቢልም ምንም ዓይነት ርዳታ እንዳልተደረገለት በምሬት ገልጿል። ኢህአዴግ «ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ» አካሂዳለሁ እያለ በብዙሃን መገናኛዎች ቢገልፅም በተ ግባር ግን ካድሬዎቹ የሚፈፅሙት ሕገ-ወጥ ጥቃት እጅግ አሳፋሪ ነው ሲል አበበ ቦጋለ ይናገራል።


# ፀናት

በአንድነት ፓርቲ ኤዲቶሪያል ቦርድ የምትታተም በፖለቲካዊ፣ማሕበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ አተኩራ በ15 ቀን አንዴ የምትወጣ ጋዜጣ

**ዋና አዘጋጅ**

አንዳርጌ መሥፍን (አድራሻ :የካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 20/21 የቤት ቁጥር (አዲስ)

ስ.ቁ 0913 05-69-42

ሪፖርተር: ዳንኤል ተፈራ

ስ.ቁ :-0911 035035

የኮምፒውተር ጽሑፍናዲዛይነር የሺ ሃብቴ

ስ.ቁ 0911 620289

**አታሚ**

ሆራይዘን ማተሚያ ቤት

**አድራሻ**

ቂርቆስ ክ/ከተማ

**ቀበሌ**

17 የቤ.ቁ 124

**የአሳታሚው አድራሻ**

ቂርቆስ ክ/ከተማ

ቀበሌ 31 የቤት ቁጥር 461 ባምቢስ ሱፐር ማርኬት ፊት ለፊት



# ፖለቲካ

# «ኢትዮጱያ ያለወደብ በታሪኳ አይታው የማታውቀው እድገት በኢሕአዴግ አሳይታለች! »

**ከብስራት ወ/ሚካኤል**

በመሠረቱ ምርጫ ማለት ካሉት የተለያዩ አማራጮች መካከል ኅብረተሰቡ ይሆነኛል፣ ይወክለኛል ያለውን ግለሰብም ይሁን ድርጅት የሚመርጥበትና የሚፈልገውን የሚተውበት ወይንም የሚያስወግድበት ሥርዓት ነው:: ለዚህም አስፈፃሚ የሚሆኑ አካላት አሉት እነዚህም:-

ከገዥው ፓርቲ /ኢሕአዴግ/ እንደ መዥገር ያልተጣበቁ ነፃ ታዛቢዎች ፣ነፃና ገልተኛ የምርጫ ቦርድ አባላት፣ ነፃ የሕግ አስፈፃሚ አካላት፣ ነፃ የፀጥታ አስከባሪዎችና እኩል የሚዲያ አጠቃቀም ወዘተ ያስፈልጋሉ:: ወይንም እነዚህ የተጠቀሱት ባንድ የምርጫ ወቅት ወሳኞች ናቸው:: እነዚህ በሌሉበት አሉ ቢባል እንኳን በተወዳዳሪዎችና በሕብረተሰቡ ዘንድ አመኔታ ባልተጣለባቸው «ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ » አካሄዳለሁ እያሉ መጮህ ከማደናገሪያናነት ያለፈ ፋይዳ የለውም:: በሌላ አባባል በነፃ ምርጫ ስበብ በብድር የተገኘ ገንዘብ በከንቱ እየበተኑ የሕዝብን ሥነ ልቦናና ሞራል እንደ መግደል ይቆጠራል:: ውሎ አድሮም እስካሁን እንደአየነው እውነቱ ሲገለጥ ትርፉ ቂምና በቀልን ማራባት ነው:: ይህ ደግሞ ባንዲት ድሃ ሀገር ከእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ነው:: እንግዲህ ይህን ያህል ለመደራደሪያነት ካልኩኝ በቅርቡ የታዘብኩትን ለወገኖች ትንሽ ላካፍል:-

ምርጫ 97 በኢሕአዴግ ከተቀለበሰ ብኋላ በ98 ዓ.ም ማለትም በቀጣዩ ዓመት የኢሕአዴግ ከፍተኛ ካድሬ ባለ ሥልጣናት መምህራንን፣ የግብርና ባለሞያ ሠራተኞችን ሌሎች የተለያዩ መ/ቤቶች ሠራተኞችን በየአዳራሹ በመሠብሰብ ላገር ልማትና አቅም ሊውል የሚችልን በሚሊዮን የሚገመት ገንዘብ በማባከን የሥራ ጊዜንና ጉልበትን አብሮ ባንድ ላይ ጨፍልቆ በመግደል ከዚህ በተጨማሪ ባለቤትነታቸው በቅጡ ያልታወቁ አምስት መፃህፍትን በማዘጋጀት የውሎ አበል ለተሰብሳቢዎች እየተከፈለ የኢሕአዴግን ኘሮግራም በማር የተቀባ ሬት እስከሚያንገሸግሸን ድረስ ካስተማሩንና ካደነቆሩን በኃላ ወዲያውኑ አባላትን መመልመላቸውን ተያያዙት:: የስብሰባው ዋና ዓላማና ታርጌትም በጅምላ ፎርም ማስሞላት ነበርና በፈቃደኝነት ሣይሆን በተለያዩ መሥፈራቾዎችና ጫናዎች ዘጠና ፐርሰንቱ ፎርሙን እንዲሞሉ መደረደራቸውን ምን ጊዜም የማንረሳው ሀቅ ነው:: ይህ ዓይነቱ አሠራርና ድርጊት ለኢትዮጱያውያን እንግዳ ነገር ከመሆኑም በላይ በዓለም ላይም ያልታየ አሥፈሪና አስነዋሪ የሆነ አካሄድ ነው:: ይህ ዓይነቱ ጅምላ ምልመላ ዛሬም ቢሆን እንደ ቀጠለ ነው:: ኢሕአዴግ የመደረሻ ግቤ ብሎ የያዘው 80 ሚሊዮን ሕዝብ ፎርም አስሞልቶ ያላንዳች ሥጋት ተቀናቃኞቼን በዜሮ አሸንፋለሁ ብሎ የተነሣ አስመስሎታል:: እህት ወንድሞችንና እናቶቻችን ሥራ የሌላቸው ነገር ግን መሥራት የሚችሉትን ከየቤታቸው ቀበሌ ስብሰባ በመጥራት እንዲሁም ቲማቲምና ሽንኩርት ከመንገድ ዳር ተቀምጠው የሚቸርችሩትን ሳይቀር እየሰበሰበ «ወጣቶች ሊግ፣ የሴቶች ፎርም ፣ያዛውንቶች.....እያለ» በመሰየም 10 ብር፣ 20 ብር፣ 30ና 50 ብር እየሰጠ የፖለቲካ መጠቀሚያ ማድረግ የዜጐችን የዘለቄታ በራስ የመተማመንና የሞራል ብቃታቸውን የሚገልና የሚፈታተን ነው:: በተለይም የወደፊት የዚች ሀገር ተስፋ ሊሆኑ የሚችሉ ወጣቶችን ያለፍላጉታቸውና ያለፍቃዳቸው የአንድ ፖርቲ አባል ሆኑ ብሎ ማስፈራራትና በተለያዩ መደለያዎች ደልሎ ፎርም ማስሞላት የከፋ ወንጀል ነው::

በዚህ አጋጣሚ አያቴ በልጅነቴ የተርኩልኝ የነበረው ትዝ አለኝ:: እንዲህ ይሉኝ ነበር:-

ኢሕአዴግ ለአገር በጐ ነገር የሚያስብ ቢሆን ኖሮ በየአዳራሹ ትንሽ ትልቅ የተማረ ያልተማረ ሣይል በጅምላ እየሰበሰበ ፎርም ሙሉ ከማለት ይልቅ የሥራ ዕድል በመፍጠር ሥራ አጡን ወጣት ሥራ ቢያሲዝ የበለጠ ተወዳጅና ተፈቃሪ በሆነ ነበር:: ከሚወደው ሥልጣን ላይም ተጣብቆ መቆየት በቻለ ነበር::

ከሰሞኑ የምርጫ ክርክር የታዘብኩትን ደግሞ ተንሽ ላካፍል:: በ97 ዓ.ም የምርጫ ወቀት አሕአዴግ ክፉኛ ሽንፈት ሲገጥመው ከተወዳዳሪዎች ከፍተኛ ካድሬዎች መሀከል አንዱ አቶ ጁነዲን ሳዶ እንደነበሩ ሁላችንም የምንዘነጋቸው አይደለንም:: ባሁኑ ወቅት እኘህ ትልቅ ባለሥልጣን የሳይንስና የቴክኖለጂ ሚኒስቴር ሚንስትር ናቸው:: የካቲት 23 ቀን ማታ በኢቴቪ ሲከራከሩ ያስተዋልኳቸው ተቃዋሚዎች:-«በታሪክም ፣ በተግባርም፣ በመልክዓ ምድር አቀማመጥም ሆነ በባህል የዓሰብ ወደብ የኢትዮጱያን አካል በመሆኑ ይገባናል:: ይህንንም በህጋዊ መንገድ መመለስ ይቻላል:: ስለዚህ ተገቢውን ዓለም አቀፍ መረጃ በእጃችን አለ» ሲሉ የኢህአዴግ ተከራካሪ የሆኑት የተከበሩ አቶ ጀንዲን ሳዶ ተቃዋሚዎች ላቀረቡላቸው ክርክር ተገቢውን መልስ መስጠት ሲችሉ ዙሪያ ጥምጥም በመሄድ « ኢትዮጱያ በታሪኳ አይታው የማታውቀውን የኢኮኖሚ እድገት በኢህአዴግ አሳይታለች:: ይህም ወደብ ሳይኖረን የታየ ዕድገት ነው!» በማለት እቅጩን ነግረውናል::

«አባቴ በአድዋ መሥዋዕትነት ክፍለዋል:: እኔም በማይጨው የድርሻዬን ተወጥቻለሁ:: ልጆቼ ግን እንጃ ? እጠራጠራለሁ :: » ይሉኝ ነበር:: ወድ ወገኖቼ ዛሬ አያቴ ይሉኝ የነበረው እውን እየሆነ ነው:: ነገስ ምን ሊከተል ይችላል? ብለን መጠየቅ እና ባገኘነው አጋጣሚ ሁሉ መነጋገር አለብን:: በተለይም በዚህ ወሳኝ የምርጫ ወቅት አገራዊ ራዕዩ እና አላማ ያለውን ፖርቲ ለይተን በማወቅ ልንመርጥ ይገባናል:: አለበለዚያ ነገና ከነገ ወዲያ ልክ እንደ አሰብ ሁሉ ድርሬደዋ፣ ሞያሌ ፣ጋምቤላ ፣ቤንሻንጉል ፣መተማና ሰቲት ሁመራ የኢትዮጱያ አካል ሆነው ስለመቀጠላቸው ምንም አይነት ዋስትናና መተማመኛ ማረጋገጫ የለንም:: ድርሬደዋ ለጅቡቲ ሞያሌ ለኬንያ ጋምቤላ ቤንሻጉል ሴቲት ሁመራ ለሱዳን የባህሪ መግዣ የማይሰጡበት ምክንያት አይኖርም:: በነገራችን ላይ የተከበሩ አቶ ጁንዲን ሳዶ « የባህር በር አያስፈልገንም ያለ ወደብ እድገት አሳይተናል» ሲሉ አስገራሚ ነው:: በዓለም አቀፍ ደረጃ ልዩ መታወቂያችን ረሃብና ስደት ሆኖ እያለና ሕዝባችን በውጭ ርዳታ መኖሩ እየታወቀ «ያለወደብ እድገት አሳይተናል» ተብሎ መነገሩ ማንን ለማታለል ነው? ከሰማዕታት ጀግኖቻችን መካከል እነ እራስ አሉላና እነአዋሎም በሕይወት ካሉትም እነ ጄኔራል ጃጋማኬሎና ሌሎችም አባቶቻችን ይታዘቡናል :: ብሎ አለማሰብም አንድም ንቀት ነው:: አሊያም ድንቁርና ነው:: የአባቶቻችን አፅም ይፋረደናል ብሎ ማሰብም በተገባ ነበር:: ነገር ግን አይንን በጨው ታጥቦ ተጨፈኑ ላሞኛችሁ ማለት ሀገራዊ ኃላፊነትን በብቃት ለመወጣት አለመቻልን በቂ ማረጋገጫ ነው:: ስለዚህ በበኩሌ ወገኖቼን ለማስገንዘብ የምፈልገው ሀገራዊ ራዕይ ያነገበውንና የመዳራሻ ግቡ ሉአላዊነቷ የተከበረ አንዲት ኢትዮጱያን ለቀጣይ ትውልድ ለማስረከብ ከኢህአዴግ ጋር የሰላም ፍልሚያ የገጠመውን መድረክን በመምረጥ ነፃነቻችንን እንጐናፀፍ !!

**ነፃነታችን በእጃችን !!**

# የአንድነት የማዕከል አመራር አባላት ከአፋር ክልል ኮሚቴ አመራር አባላት ጋር ውይይት አካሄዱ

የካቲት 16 ቀን 2002 ዓ.ም ሦስት አባላት የሚገኙበት የአንድነት የማዕከል አመራር አባላት ከአፋር የአንድነት ኮሚቴ ሥራ አስፈጻሚ አባላትና የፖርላማ ዕጩ ተመራጮች ጋር በአዋሽ ፈንታሌ ከተማ ውይይት አካሂደዋል:: ውይይቱ ያተኮረው ምርጫውን በተመለከተ የአንድነት እንቅስቃሴ ምን እንደሚመስል በኮሚቴው አባላትና በእዕጩ ተመራጮች ከአካባቢው ባለሥልጣናት እየደረሰባቸው ያለ ተጽዕኖ ማስፈራራትና ወከባ ላይ ነበር:: ውይይቱ በሚካሄድበት ጊዜ የወረዳው ባለሥልጣናት ዙሪያውን በማንዣበብ ውይይቱን እንዲከታተል በቅርብ ሰው (ሰላይ) በማስቀመጥ ለማስፈራራት ሞክረዋል:: የአንድነት አባላትና ዕጩ ተመራጮችን የለመድነው ነው በማለት በረጋ የተላከውን «ቃል አቀባይ» በመሀከላቸው አስቀምጠው ተወያይተዋል:: የአባላቱ የትግል ተነሳሽነትና የአሸናፊነት ስሜት ከፍተኛ ነበር:: በበኩላቸው ከማዕከል አመራርና የሞራል ከተቻለ ደግሞ የፋይናንስና የማቴሪያል ድጋፍ እንዳይለየን አደራ ብለዋል::

በስብሰባው ላይ የተገኙ የማዕከል አመራር አባላት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ምክትል ሊቀመንበርና የውጭ ጉዳይ ኃላፊ፤ ዶ/ር ኃይሉ አርአያ ም/ሊቀመንበርና የጥናትና ምርምር ጉዳይ ኃላፊ አቶ አሥራት ጣሴ የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ እንዲሁም አቶ ከተማ አምዴ የምሥራቅ ቀጣና አስተባባሪና ከምስራቅ-ምዕራብ ቀጣና ዋና ፀሐፊ ናቸው:: ከክልሉ ኮሚቴ አቶ ሑመድ አፍዓሶ ዓሊ እንዲሁም የዞኑ ኃላፊና የሐገር ሽማግሌ አቶ ሙሣሐላቶ ሐንዴ ተገኝተዋል:: በተጨማሪም 3 የፓርላማ ዕጩ ተወዳዳሪዎች እንዲሁም 15 የክልል ም/ቤት ዕጩ ተወዳዳሪዎች ተገኝተዋል:: ከ15ቱ አንዷ ሴት ናት::



# ያለ ሠላም . .

ከገፅ 5 የዞረ

ገፅታ በሆንም ለብዙዎቻችን ግን የሚዋጥ አልሆነም:: ላንዳንዶቻችን ሰላማዊ ትግልን የሚጣፍጥና ውጣ ውረድ የሌለበት ወይንም የሁለት ቡድኖች የእግር ኳስ ጨዋታ ይመስለናል:: ግን አይደለም:: ትግሉም ባንድ ወቅት ተጀምሮ ባንድ ጊዜ የሚቋጭና ሁሉም ነገር አልጋ ባልጋ የሚሆንበት አይደለም:: ይልቁንም የግዕዙ ቃል «ሰላም ማለት ፍቅር አንድነት ትሁት . . .» ስለሚል ለሁሉም በሩ ክፍት በመሆኑ ለግል ጥቅምና ዝና የሚሯሯጡ ስለሚስገበገቡበት ትግሉ እጅግ እልህ አስጨራሽ ነው:: እንደ ትጥቅ ትግለም ባንድ ጊዜ ሞሽናፊው ኃይል የሚቋጭ አይደለም:: ሌላው መታወቅ ያለበት ሠላማዊ ትግል ያንድ ወገን ሃብት ብቻ አለመሆኗን ነው:: በሁለቱም ወገን ስጥቶ የመቀበልንና የመቻቻልን መርህ መቀበል ሲቻል ነው ሰላም የምትሰፍነው:: መቻቻል ሲባልም ደካማው ጉልበተኛውን አዝሎ እንዲኖር ሳይሆን በተወሰነ መልኩም ቢሆን ሰጥቶ የመቀበል ጥበብን መካነን ይጠይቃል:: በተለይም የሀገር ጉዳይ ከሆነ ማስተዋል፣መረጋጋትን የግድ ይላል::

ኢህአዴግ ግን መረጋጋትንና መቻቻልን ወይንም የሰጥቶ መቀበል መርህን የሚያውቀው እሱን መሸከም እስከተቻለ ድረስ ብቻ ነው:: በሌላ አባባል የሰላማዊ ትግልን አስፈላጊነትና የመድብለ ፓርቲን ጠቃሚነት የሚቀበለው እሱን ማጀብ እስከተቻለ ድረስ እንጂ የሐሳብ አማራጭነትንና የፖሊሲ ለዩነትን አያምንም:: ይህንን ግብሩንም በተደጋጋሚ ሁኔታ በተግባር አሳይቷል:: የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት አራምዳለሁ ቢልም ከተሌቪዥንን ጨኸት ያለፈ በተግባር ያሳየው ነገር የለም:: መርሁ «አብዮታዊ ዴሞክራሲ» በመሆኑ ግብርና በኮ ሚኒዝም ሥርዓት የተገራና የተቃኘ ስለሆነ ሁሉም ነገር የሚጠናቀቀው በውይይትና ሰጥቶ በመቀበል ሳይሆን በኃይልና በጉልበት ነው:: ምርጫ 97ትን ማስታወስ ብቻ በቂ ነው::

አንዳንድ አዛውንቶች 97ን በማስታወስ ሰላማዊ ተግል በኢትዮጵያ እንደማይሠራ አጥብቀው ይመክራሉ:: «አርፋችሁ ተቀመጡ የእሳት እራት መሆን ነው» በማለት በሰላማዊ ትግል ለውጥ ማምጣት እንደማይቻል ይናገራሉ::

እኛ ደግሞ ርግጠኛ ሆነን በሰላማዊ ትግል ለውጥ ማምጣት ይቻላል፣የትጥቅ ትግሉን ለጎሺ ዘመን ሞክረነዋል:: ምንም አይነት ለውጥ ማምጣት ግን አልቻልንም:: እስቲ ደግሞ ጊዜው የሚጠይቀውን የሰላማዊ ትግልን ፈር ተከትለን እንየው፣እንሞክረው፣በማለት ስንሞግታቸው የጦር ኃይሉን የፖሊስ ሠራዊቱን የጠቅሉና «እሳት የታጠቀን ኃይል እንዴት በብዕር ማሸነፍ ይቻላል» በማለት እነሱ በበኩላቸው ይከራከራሉ:: እኛም መልሰን «ኢህአዴግ እሳት ቢታጠቅም በውሃ እናጠፋዋለን:: ሕዝብ ባንድ ልብ ከተነሳ የሀምሌ ጎርፍ ነው፣ይጠራርጋል፣ደግሞስ ሠራዊቱ የሕዝብ ልጅ አይደለምወይ? በማን ላይ ነው የሚተ ኩሰው?እስከመቸስ የገዛ ወገኑን እየገደለ የአምባ ገነኖች መሣሪያ ሆኖ ይኖራል?» በማለት ስንጠይቃቸው አሁንም መልሳቸው የታጠቀን ኃይል በታጠቀ ኃይል እንጂ በሰላማዊ ትግል ከሥልጣኑ ማውረድ አይቻ ልም የሚል ነው::

አዛውንቶቹ እንዲህ አይነቱን ክርክር ሲያነሱ በጭፍን ተነስተው አይደለም:: ካለው ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት ኢሕአዴግ የሰላማዊ ትግሉን ጎራ ለማዳፈን እያራመደ ያለውን እኩይ ተግባር በመመልከት ነው:: አዛውንቶቹ ያልተገነዘቡት ቁምነገር ግን ኢሕአዴግ የትጥቅ ትግሉን ደህና አድርጎ ያውቀዋል፣አያስፈራውም፣የሚፈራውና የሚያስደነግጠው የሰላማዊ ትግል ስልት ነው:: ይህንን ቀና መንገድ እናለማምደው ነው የምንለው አቋማችንም ዓላማተንም ይኸው ነው:: በዚህ ሥልጡን ዘመን የትጥቅ ትግል በምንም መመዘኛ አማራጭ ሊሆን አይችልም:: በርግጥ ኢህአዴግ በብዙሃን መገናኛዎች «ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ አካሂዳለሁ» እያለ ቢሰብክም በተግባር ግን የሰላማዊ ትግሉን መሥመር ለማሳት በሽብርተኝነት ስም ሽብር እየነዛ የሕዝብን ስሜት ማሸማቀቁ እውነት ነው:: ይህም ባንድ እጁ ብዕር በሌላው እጁ ጠመንጃ የጨበጠ ለመሆኑ በቂ ማረጋገጫ ነው:: ይሁን እንጂ ይህንን ኃላፊነት የጎደለውን ተግባሩን ማጋለጥ እንጂ ከሰላማዊ ትግሉ አንድ ርምጃ በራቅን ቁጥር እየተ ከተለ ያሳድደናል እንጂ ኃላፊነት ተሰምቶት በሕዝብ ኑሮ መጎሳቀልና መቆርቆዝ ይቆጫል ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው:: አሥራ ስምንት ዓመት አየነው፣ጠበቅነው የወደፊት ራዕዩም ከስታሁኑ የተ ለየ እንደማይሆን የታወቀ ነው:: ምክንያቱም መርሁ «አብዮታዊ ዴሞክራሲ» ነውና

ሌላው ብዙ አዛውንቶችን በሰላማዊ ትግል ዙሪ ያ የሚያነጋግራቸው ጉዳይ የወ/ሪት ብርቱካን በጭካኔ የእድሜ ልክ እስራት ሰለባ መሆኗ ነው:: የገዥው ፓርቲ እሷን ሲያስርም በቅድሚያ ታሳቢ ያደረገው ሁሉም «እሷን ያየህ ተቀጣ!» በማለት ከሰላማዊ ትግሉ እንዲያፈገፍግና ሰጥ ለጥ ብሎ እንዲገዛ ለማድረግ ነው:: ግን ኢህአዴግ ታሪክ ይቀር የማይለው ስህተት ፈፀመ:: ዛሬ ብርቱካንን ብቻዋን አስሯታል:: ይዘገያል እንጂ ነገና ከነገ ወዲያ የሷን የሰላም አርማ የሚያነሱ በሺዎች የሚቆጠሩ ብርቱካኖችን ኢትዮጵያ ታፈራለች:: ያንጌ ስንቶቹን ጋሮ ዕድሜ ለክ ይፈርድ ይሆን?

ኢህአዴግ ብርቱካንን ለመፍታት አሁንም ጊዜው አረፈደበትም:: ደግሞ ደጋግሞ በማሰብ ሊፈታት ይገባል:: ዜጎችን በማሰርና በመግደል ሥልጣን ላይ የሚቆይ ቢሆን ኖሮ ደርግ አንፈራጦ መቆየት በቻለ ነበር:: ይህንን ታሪክ ጠንቅቆ የሚያውቀው ኢህአዴግ ከደርግ ወንበር ላይ በመቀመጡ ብቻ ግብሩንም አብሮ መውረሱ በጣም የሚያሳፍርና የሚያስተዛዝብ ነው:: ሥልጣንምኮ የሚጣፍጠው በሕዝብ ዘንድ አመኔታ ሲኖርና ግርማ ሞገሥ ሲያጎናፅፍ ነው:: ተጠልቶ መግዛት ግን የታሪክ ጥላሸትን መቀባት ነው:: በተረፈ ግን እኛ እያልን ያለነው፣ሕዝብም የሚመኘውና የሚፈልገው በሰላማዊ መንገድ ለውጥ ማምጣት ነው:: ሕይወት ሳይጠፋ፣ያገር ንብረት ሳይወድም፣ቂምና በቀል ሳንወራረስ ሥልጣን በሰላማዊ መንገድ ካርዱን ወደ ሌላው የሚሽጋገርበትን ሥርዓት መገንባት ነው:: ለዚህ የተቀደሰ ተግባር ስንንቀሳቀስ ደግሞ በእያንዳንዱ ርምጃችን የሰላም ጠንቆች ይፈታተኑናል:: አንድም በራሳቸው አቅም አለያም በኢሕአዴግ ጃዝ ባይነት! ያምሆን ይህ ሰላም የዕ ድገታችን ዋስትና ነውና ሁላችንም ለሰላም ዘብ እንቁም::

# የመድረክ እጩ ተወዳዳሪ . . .

ከገጽ 1 የዞረ

ሰርዝንሃል ተባልኩኝ ሲሉ ለፅናት ጋዜጣ ገልፀዋል::

በ1997 ምርጫ ቅንጅትን ወክለው ተወዳድረው በማሸነፍ የተ ወካዬች ም/ቤት አባል በመሆን እያገለገሉ እንደሚገኙ የገለፁት አቶ አዕምሮ የክልሉ ምርጫ ቦርድ ወኪሎች ፍትዊ ባልሆነ መንገድ ተገቢውን መስፈርት አሟልቼ እንዲሁም መታወቂያ አቅርቤ እያሳየኋቸው በተጨማሪም ተወላጅ መሆኔን የሚገልፅ ሰው ምስክር ላቅርብ እያልኳቸው አይሆንም በማለት እንደተሰረዝኩ ነግረውኛል:: በምርጫም እንዳልሳተፍ ተደርጌያለሁ ብለዋል:: አያይዘውም ምርጫ ቦርድ አሳውቄ ካልሆነም እስከ ፍርድ ቤት ድረስ በመውሰድ መብቴን አስከብራለሁ ሲሉ ለፅናት ጋዜጣ ተናግረዋል::

## ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ ...

ከገጽ 1 የዞረ

የአራት ወሩን የስራ ሪፖርት ማዳመጥ፤ የአመራር ለውጥ መደረግ ስላለበት በቀጣዩ 4 ወር አመራሩን የሚረከቡትን መምረጥ ዋናዎ ቹ ነበሩ::

ባለፉት አራት ወራት የተሰሩትን የስራ ሪፖርት ማዳመጥ በተመለከተ ከጥንካሬ ዎች ትምህርት በመውሰድ መድረክ ተጠናክሮ ወደ ምርጫው እንዲገባና ስራውን አጠናክሮ እንዲቀጥል ተወስኗል:: የተከሰቱ ድክመቶችን በተመለከተ ግምገማ ተካሂዶ የተሻለ ስራ ለመስራት ካለፈው በመማር የአመራር ጥንሬ አስፈላጊ መሆኑና እያንዳንዱ የመድረክ ድርጅት በግሉ ትኩረት በመስጠት የመድረክን ዓላማና ግብ እንዲሳካ ለማድረግ በመስማማት ተጠናቋል::

የአመራር ለውጥ መደረግን በተመለከተ ለቀጣዩ አራት ወራት መድረክን የሚመሩ ሁለት እጩዎች የቀረቡ ሲሆን (ፕ/ር በየነ ጴ ጥሮስና አቶ ገብሩ አስራት) ፕ/ር በየነ በአብላጫ ድምፅ ለቀጣዩ አራት ወር በሊቀመንበርነት ለመምራት ተመርጠዋል:: ተ ቀዳሚ ም/ሊቀመንበር ደግሞ አቶ ገብሩ አስራት ሆነዋል::

አቶ ገብሩ አስራት ይመሩት የነበረውን የሕዝብ ግንኙነት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ተ ረክበዋል:: መድረክ ባለፉት አራት ወራት በእጩ ምደባ ላይ የገጠሙ ችግሮችን በውይይትና ሰጥቶ በመቀበል መርህ እየተመራ በመፍታት በብቃት እንደተወጣና ወደ ከፍተኛ ደረጃ እንደተሸጋገረ የመድረክ የሕዝብ ግንኙ ነት የሆኑት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ለፅናት ጋዜጣ ገልፀዋል::

በተጨማሪም በድርጅቱ ፋይናንስ ሁኔታ ላይና በእጩ ምደባ ላይ ትሬታ በነበራቸው ላይ ውይይት ተካሂዷል::

ጠቅላላ ጉባዔውም ይሄንን በተመለከተ ቀጣዩ ስራ አስፈፃሚው ጥናት አካሂዶ የጥናቱን ሪፖርት በሦስተ ኛው ጠቅላላ ጉባዔ እንዲቀርብ ተወስኗል::

# የዓረና

ከገፅ 1 የዞረ

አቶ ገብሩ አሥራት ገልጸዋል::

የካቲት 22 ቀን 2002 በአቶ አረጋዊ መጠጥ ቤት ያመሹት ሰ ዎች በዘጠኝ ሰዓት ላይ ረብሻ አስነስተው የድርጅቱን እቃ በመሰባበር ጩኸት ሲበረክት አቶ አረጋዊ « ምንድ ነው ብለው ከመኖሪያ ቤታቸው ሲወጡ በጩቤ ደጋግመው በመውጋት የተገደሉ መሆናቸውን ሊቀመንበሩ አስታውቀዋል::

የመድረክ አባል የሆነው ዓረና በትግራይ ክልል ካስመራቸው የተ ወካዬችና የክልል እጩ ተወዳዳሪ ዎች መካከል ሟቹ አቶ አረጋዊ አንዱ ሲሆኑ የስድስት ልጆች አባት እና ባለትዳር ነበሩ::

# የጉራጌ ዞን

ከገፅ 7 የዞረ

እንዲሁም ለአንድ ምርጫ ብቻ ተ ብሎ በሚሠራ ስራ ሣይሆን ዘላቂነት ያለው የፖለቲካ ፕሮግራም በመንደፍ ሕዝቡ ውስጥ ተገብቶ ከተሠራ በእርግጥም የለውጥ ጊዜው ቅርብ ነው ማለት እንችላለን::

## 4 ተቃዋሚዎች ሊከተ ሉዋቸው የሚገቡዋቸው የምርጫ ቅስቀሣ መንገዶች ምን ምን መሆነ አለባቸው?

የጉራጌ ብሔር ሕብረተሠብ እንደ ኢትዮጵያ ብሔሮች ሁሉ ኢህአዴግን ለመቃወም የሚያስችሉ በርካታ የጋራ ጉዳዮች ቢኖሩትም የሕብረተሰባ አባላት ከሌላው ኢትዮጵያዊ በተለየ መንገድ ተጐድተናል ብለው ያምናሉ ለዚህም የሚያቀርቧቸው ምክንያቶች አሉ::

## 1. ዴሞክራሲና የዜጐች እኩልነት

ሕዝቡ ከሌላው ሕዝብ በተለየ ሁኔታ ተንቀሣቃሽና በንግድ ስራ ዎች ውስጥ የተሠማራ በመሆኑ በባህሪው ጠንካራ ዴሞክራሲያዊና በእኩልነት ላይ የተመሠረተ የፖለቲካ ስርዓት መፈለጋቸው ነው:: አብዮታዊው የኢህአዴግ የፖለቲካ ስርዓት ደግሞ የዚህን ሕዝብ ፍላጐት ሊያሟላ አይችልም::

(ወደ ገፅ 8 ዞሯል)

## ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ

# ያለ ሠላም ዕድገት የለም

ከአንዳርጌ መሥፍን

__ሠላም__ ስለ ሠላም ብዙ መባል ብዙ መሰበክ ያለበት ይመስለኛል:: ኅብረተሰባችን ስለ ሠላም ያለው ግንዛቤ እጅግ የቀዘቀዘና የደበዘዘ ነው:: ስለሠላም ሲነገር በአእምሯችን ውስጥ የሚመጣው ያላንዳች መስዋዕትነት ከሰማይ እንደ ወረደ መና ዳቦ የሚገመጥ የሚመስለን ጥቂቶች አይደለንም:: ለዚህም ነው:: ስለሠላም ደግመን ደጋግመን መስበክና መጮህ አለብን የምንለው::

__ሠላም__ የግዕዝ ቃል ሲሆን ትርጓሜው «አማን፣አንድነት፣ደህና፣ጤና፣ፍቅር፣ትሁት» ማለት ነው:: ሠላም ለሰው ልጅ ብቻ ሣይሆን ላዝርዕት፣ለዕፅዋት፣ለእንስሳት ጭምር ዋስትና እንደሚሆን የግዕዙ ቃል ያስረዳናል:: ከዚህ ፅንሰሐሳብ ስንነሳ አንድን ሰብል ወይንም አዝርእት ወስደን ብንመለከት እድገቱን የሚያቀጭጩ ሁኔታዎች መኖራቸው ግልፅ ነው:: ለምሣሌ:-

አንድ ሰብል አፈሩና አየሩ የማይስማማው ከሆነና በቂና ተመጣጣኝ ዝናብ ካላገኘ የሚጠበቅበትን ምርት አይሰጥም ወይንም ለሰው ልጅ ጠንቅ የሚሆኑ ሰላም ነሽ እፆችን ሊያፈራ ይችላል:: ከስንዴ መሀከል ጭንቅላትን የሚያዞር እንክርዳድን ሊያፈራ ይችላል:: እንዲሁም ጥላሸት የሚቀባ ጎስ የሚባል አለ:: የተለያዩ ፀረ-ሰብል አረሞችንና ተባዮችንም መርሳት የለብንም:: እነዚህ ሁሉ ሰብሉን ወይንም አዝመራውን ሰላም የሚነሱና ዕድገቱን የሚገቱ የምርቱን ጥራትና መጠን የሚቀንሱ ናቸው:: በተመሳሳይ ሁኔታ በማኅበረሰባችን ውስጥም ለሰላም ጠንቅ የሚሆኑ እንክርዳዶችና ጎሶች ወይንም አራሙቻዎች መኖርቸውን ማንም አይክድም:: ከዕፅዋት መሀከልም ለሌላው ዛፍ ምቹ የማይሆኑ እንዳሉ እንረዳለን:: ሁሉም ዛፎችና ዕፅዋት ጠቃሚዎች ናቸው ማለት አንችልም:: እሾሆቻቸው ዓይኖችን መንጥቀው የሚያስቀሩ እፅዋት አሉ:: ግመር፣ቀንጠፋ በመለስተኛ ደረጃም ቢሆን ፍሬአቸው ጣፋጭ በመሆኑ ባናማርራቸውም አጋምና ቀጋ በተቧጣጭነታቸው ቀላል የሚባሉ አይደሉም:: ከነ ተረቱ «ካጋም የተጠጋ ቁልቋል ሲያለቅስ ይኖራል!» ይባላል ባንፃሩም እንደ ዝግባ ወይራ፣ጥድና ዋንዛ ዛፎች የተከበሩ ናቸው:: እንዲሁም ጥላው ሳይቀር ከፀሀይ ቃጠሎና ከሀይለኛ ወኾቦ የሚከላከል የዋርካ ዛፍ በጥንካሬውና በዕድሜ ጠገብትነቱ የታወቀ በመሆኑ በሱ ላይ ጨክኖ መሳሩን የሚያነሳ የለም:: ቅርስን እንደማጥፋት ይቆጠራል:: በሌላ በኩልም እንደብሳና ያሉ ነቃፐችም አሉ:: «ከነተረቱ ብሳና ይነቅዛል ወይ ቢሉት፤ለእንጨቱ ሁሉ ማን አስተማራቸው» ይባላል::

በማኅበረሰባችን ውስጥም እንደ ብሳና ዛፍ ሐሳባቸው ለምንም ነገር የማይጠቅም የነቀዙ ግለሰቦች አሉ:: እንደነዚህ ያሉ ግለሰቦች ሰላምን ለመገንባት በሚያደርገው ጥረት በአፍራሽ መልኩ በመሰለፍ የክፋት እንክርዳድን በመዝራት ጭንቅላትን በማዞር የሰላምን አቅጣጫ ያስታሉ:: የሚፈልጉትም ይህንኑ ነው ደስ ይደላቸው::

ሰላም እንስሳትን በተመለከተም ብዙ ሊባልለት የሚችል ነው:: አእዋፋትን የጥይት ድምፅ ያሸብራቸዋል፤ያስጨንቃቸዋል፤አካባቢያቸውን ለቀው ይሰደዳሉ:: እንዲሁም ባንድ በረት ውስጥ አንድ በጥባጭ ኮርማ ካለ መንጋው ተረጋግቶ አያድርም:: ሁልጊዜም በረቱ ሰላም አጥቶ እንደ ተበጠበጠና እንደ ታመሰ ነው የሚነጋው::

በሌላው ደምና ሥጋ የሚኖሩ ሠላም አደፍራሾች አራዊትንም መርሳት የለብንም:: ጅብ፣ነብር አንበሳ ተኩላና ቀበሮ ሌላውን ሰላም መንሳታቸው ብቻ ሳይሆን እነሱም ካላደኑ በስተቀር መኖር ስለማይችሉ ሰላም የላቸውም:: ባጭሩ ዓላማችን ባዳኝና በታዳኝ የተሞላች ነች:: እነዚህን ሁሉ እየተቆጣጠረ በበላይነት ወደ ሚመራው የሰው ልጅ ስንመለስ ከላይ ከተጠቀሱት ሥጋ በል አራዊት የተለየ ሆኖ አናገኘውም:: በጥብጥንና የሰላም መደፍረስን በትንሹም በትልቁም ጦርነት እየለኮሱ ያገርንና የሕዝብን ንብረትና ሕይወት የሚያጣፉ መሪዎች ትናትም ነበሩ፤ዛሬም አሉ፤ነገም ይኖራሉ:: ፐ/ሬ መንግሥቱ ኃይለማርያም በመሪነታቸው የሰላምን ሥንቅ ሳይሰንቁ ወጣቱን በነጭ ሽብርና በቀይ ሽብር አቧድነው «አብዮታዊት እናት ሀገር ወይንም ሞት! ሁሉም ነገር ወደ ጦር ግንባር!» በማለት አገርንም ንብረትንም ትውልድንም አጥፍተው ጠፉ:: ዛሬስ ስለ ሠላምና ስለሰላማዊ ትግል ምን እንላለን? ካለፉት ችግሮቻችንስ ምን ያህል ተምረናል? ስንቶቻችንስ ስለሠላማዊ ትልግ ቆርጠን ተነስተናል? እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ እንሞክር::

በደርግ እግር የተተካው ኢህአዴግ ሰላምንና ሰላማዊ ትግልን በጋዜጣ፣በሬዲዮና በቴሌቪዥን እንጂ በተግባር አያውቃትም ማለት ይቻላል:: በትጥቅ ትግል ተኮትኩቶ ያደገ በመሆኑና ሥልጣን ላይ የወጣውም በጦርነት አሸንፎ ስለሆነ ሰላማዊ ትግል ለራሱ የምትጐመዘዝ እንጂ እንደ ማር የምትጣፍጥ አይደለችም:: በዚህ የተነሳም ገና ከውጥኑ «መንገዱን ጨርቅ ያድርግላችሁ» ከሚለው ምፀታዊ አነጋገር ጀምሮ ዛቻና ማስፈራራት እንዲያም ሲል ወንጀል እየፈጠረ ሰላምን ንጹሐን ዜጎችን መቅጣት አንዱን ጐሳ ከሌላው ጐሳ ማናከስ እንዲሁም «መንግሥት በሃይማኖቶች መሃከል ጣልቃ አይገባም» በሚል ሽፋን የሃይማኖት ግጭቶችን በወቅቱ ከመፍታት ይልቅ ከዳር ሆኖ ተመልካች በመሆን በሀገሪቱ ውስጥ ሰላም እንዳይሰፍንና ሰላማዊ ትግል አብቦ እንዳያፈራ ጠውልጐ እንዲቀር በዚህም የግዛት ዘመኑን ለማራዘም እየጣረ ይገኛል::

ለተቃዋሚ ፓርቲዎች በሩን ገርበብ ያደረገ በመምሰል በተግባር ግን ደህንነቱን የፖሊስና የጦር ኃይሉን እንዲሁም የብዙሃን መገናኛዎችን በቁጥጥሩ ስር አድርጎ በዴሞክራሲ ስም ሲነግድ በሌላ በኩል ግን ሰላም የጠማው ሕዝብ ሐሊናው እየቆሰለ ይገኛል:: ዛሬ እንደ ኢህአዴግ ደረቅ ፕሮፖጋንዳ እንንዛ ካላልን በስተቀር በሕዝባችን ውስጥ የተረጋጋ ሰላም የለም የኑሮ ውድነት የትራንስፖርት ችግር ሠራተኛው ከሥራ እባረራለሁ በሚል ስጋት እየባነነ ይገኛል:: ከሁሉም በላይ ያለፈቃዱና ያለ እምነቱ የኢህአዴግን ያባልነት ፎርም እንዲሞላ በጅምላ ጠመቃ ስልት ማስቀገዱ ረፍት የሚያሳጣ የሕሊና ጫና ፈጥሮበታል:: ፎርም ለመሙላት ፈቃደኛ ባልሆኑ ዜጎች ላይ የቀበሌና የወረዳ ካድሬ ባለሥልጣናት በፈጠራ ክስና ውንጀላ ስለሚያምሷቸው እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ እየበረገገና እየባነነ የዕለት ሕይወቱን ለመግፋት ተገዷል::

በተለይም ከ97 ዓ.ም ሕዝባዊ ምርጫ ወዲህ ገዥዎቻችን ሰላም አጥተው ሌት ተቀን እየባነኑ ናቸው:: ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ሰላማዊ ትግል ጨርሶ ተዳፍኗል ባይባልም በኢህአዴግ የጠነነ ሐሳብ ምክንያት ሰላም ጠውልጋለች ማለት ይቻላል:: ዛሬ አገራችን ዘርፈ ብዙ ችግሮች ተጋርጠውባታል:: ይህንን ሀቅ ከኢህአዴግ በስቀተር የሚክድና የሚያስተባብል የለም:: የሀገሪቱን ችግርለመፍታት ደግሞ በኢህአዴግ ብቻ የሚታሰብ አይደለም:: የእያንዳንዱን ዜጋ ተሳትፎ የሚጠይቅ ተግባር ነው:: ለዚህ ደግሞ ሰላማዊ ትግል ወሳኝ ነው:: በረግጥ በሃገራችን በሠላማዊ ትግል ሥልጣን ተይዞ ስለማይታወቅ ሕዝባችን ለሰላማዊ ትግል የሚሰጠው ዋጋና ግምት እጅግ አነስተኛ በመሆኑ ገዥው ፓርቲ በሥልጣን ላይ አንፈራጦ እንዲቀመጥና ዕድሜውን እንዲያራዝም ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮለታል:: ባንፃሩም የሕዝቡ ኑሮ ከዕለት ወደ ዕለት እያሽቆለቆለ ይገኛል::

አንዳዶቻችን ደግሞ ለሰላማዊ ትግል ዋጋ የምንሰጥ እንመስልና የግል ስሜታችንን ይዘን ስለምንቀላቀል እለቱን ዳቦ ለመግመጥ እንሻለን:: ይህንን ስናጣ አንጃ በመፍጠር የጥላቻ መርዝን በመርጨት የሰላማዊ ትግሉን ጎራ እንበጠብጣለን፤እናምሳለን፤በዚህ አጋጣሚ ኢህአዴግ ተጠቃሚ ይሆናል::

ኢሕአዴግ ሥልጣን ላይ ከወጣ ጀምሮ በስመ ሰላማዊ ትግል በየዕለቱ የሚፈጠሩት የፖለቲካ ፓርቲዎች እጅግ በርካታዎች ናቸው:: እንዳቸውም ግን ችግር ሲፈቱ አልታዩም:: አፈጣጠራቸውም ችግር ለመፍጠር እንጂ ለመፍታት አይደለም:: በመሆኑም አንዳንዶቹ ጧት ተፈጥረው ማታ የሚፈርሱ ናቸው:: አንዳንዶቹም ርስበርሳቸው ተጠላልፈው በራሳቸው ጊዜ ከስመዋል:: ሌሎች ደግሞ በሕዝብ ስም እየማሉ በተግባር ግን የኢህአዴግ ምርኩዝ በመሆን የሚያገለግሉ ናቸው::

ከተቃዋሚ ፓርቲዎች መሀከል ቅንጅት ብቻ በ97 ዓ.ም ምድር አንቀጥቅጥ ለውጥ ማምጣት ችሎ ነበር:: የሰላማዊ ትግልን ምንነትም በቅጡ አሳይቷል:: ወይንም በካርድ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል ግንዛቤን አስጨብጧል:: ምን ይሆናል ታዲያ ኢህአዴግ በተለመደ የቆረጣ ስልቱ ቆርጦ አስቀርቶታል:: በሕዝቡ ዘንድም «ያልነው አልቀረም!» የሚል ፀፀትን አሳድሯል::

የቅንጅት መሪዎች በድል አድራጊነት ወደ ቤተ መንግሥት መግባት ሲገባቸው ባሳፋሪ መልኩ ተጋፈው ቃልቲ እስር ቤት ታጎሩ:: «የሕዝቡ ድምፅ ይከበር!» ብለው የጮሁ ወጣቶችም ተጋፈው በተለያዩ እስር ቤቶች ተጋዙ:: የብዘዎቹ ሕይወትም ባሳዛኝ መልኩ ተቀጠፈ:: በቀላሉ የማይገመት ንብረትም ወደመ:: ይህ ክስተትም የሰላማዊ ትግሉ አንዱ

**(ወደ ገፅ 4 ዞሯል)**

# መድረክ

## «ኢህአዴግ አሰፈንኩ የሚለው ዴሞክራሲ በልኩ የተሰራ ጥብቆ ነው!»

ዶ/ር መረራ ጉዲና

የካቲት 20 ቀን ነበር:: መርካቶ እንደወትሮዋ ሁሉ በትርምስና ግርግር ተሞልታለች:: መርካቶን ለመግለፅ የእውቁን ባለቅኔ የሎሬት ፀጋዬ ገ/መድህንን «አይ መርካቶ» ማስታወስ እንጅ እንዴትስ ይገልፁታል? ወደ አዲስ ከተማ ት/ቤት ስደርስ የት/ቤቱ አዳራሽ ጢቅ ብሎ ሞልቶ ሰው ቁሞ ነበር:: ይከታተል የነበረው ይህም ኢትዮጵያዊ ጨዋነት የተንፀባረቀበት እንደነበር ለመረዳት ተችሏል::

ሰባት ሰዓት ተኩል የመድረክ መሪ የነበሩት ወ/ሮ ላቀች ደገፋ የአንድነት ፓርቲ የሴቶች ጉዳይ ኃላፊና በ2002 ምርጫ ተወዳዳሪ ናቸው:: በመሃል መፈክሮችን እያሰሙና ቁም ነገር እየሰነዘሩ ከቆዩ በኋላ የመክፈቻ ንግግር እንዲያደርጉ የተከበሩ ዶ/ር መረራ ጉዲናን ጋበዙዋቸው::

የፖለቲካ ሳይንስ ምሁር የሆኑት ዶ/ር መረራ ጉዲና ስለመድረክ ተጠይቀው ሲመልሱ «መድረክ እየተባለ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የሚዘመትበት ለምንድን ነው?» አሉ:: «አሁን ሁለት ጐራ ተፈጥሯል አንደኛው ኢህአዴግ የፈጠረው አምባገነናዊ ስርዓት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አዲሲቷን ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመፍጠር የተፈጠረው መድረክ ነው:: መድረክ ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን ዕውን ለማድረግ የተፈጠረ ነው:: እኛ የምናውቀውና ኢህአዴግ አስፈንኩት የሚለው ዴሞክራሲ በራሱ ቁመት ልክ የተሰራ ጥብቆ ነው::» በማለት ማብራሪያ ሰጡ::

ዶ/ር መረራ ጉዲና በመግቢያ ንግግራቸው አምርረው የተናገሩት እጩዎች እንዲመዘገቡ ያለው ውጣ ውረድ ቀላል እንዳልነበረ ገልፀው አብዛኛው የገዥው ፓርቲ ቁራኛ የሆኑትና ለገዥው ፓርቲ የተሰለፉ ኃይሎች የመኪናችንን መስታወት ጭምብል ለብሰው ሰብረዋል:: ይሄን ተቋቁመን ግን በመላው ኢትዮጵያ እጩዎችን ለማስመዝገብ ችለናል ሲሉ የስብሰባው ተሳታፊዎች የድጋፍ ጭብጨባ አድርገዋል::

በመሀል አንድ ያስተላለፉት መልዕክት ታዳሚውን ፈገግ አሰኝቷል:: ለአጨዋችነት የገቡ የፖለቲካ ፓርቲዎች ስላሉ ድምፃችሁን እንዳታበላሹ:: መቸም ምርጫ ሲመጣ ብቅ የማይል ፓርቲ የለምና ነው:: አዲሲቷን ኢትዮጵያ የመፍጠሪያው ጊዜ አሁን ነውና ልትደግፉን ይገባል» ብለው ንግግራቸውን ቋጭተዋል::

በአዲስ ከተማ ት/ቤት ስብሰባ ላይ መድረክ በአዲስ አበባ ላይ ያቀረባቸውን እጩዎች ለሕዝቡ አስተዋውቋል:: እጩዎች ስማቸውንና የት/ምህርት ደረጃቸውን በመግለፅ ትውውቅ አድርገዋል::

እጩዎች ሲተዋወቁ ድንገት መብራት ጠፋ ወዲያውኑ ብዙ ሳይቆይ የስብሰባው አደራጆች ጀነሬተር አስነሱ:: (በነገራችን ላይ መድረክ ባካሄዳቸው ሁለት ስብሰባዎች ላይም መብራት ተቋርጧል:: ለምን ይሆን?)

በቀጣዩ መርሃ-ግብርም «የሴቶች መልዕክት» በወ/ት ልዕለና ጉግሳ ቀረበ:: በዕለቱ የአንድነት ፓርቲ ሊ/መንበር ወ/ት ብርቱካ ሚደቀሳ የታሰረችበት 14ኛ ወር ነበር:: «ብርቱካን ብርቱ ዳኛ እንጅ ወንጀለኛ እንዳልሆነች አሳሪዎቿ ጠንቅቀው ያውቁታል» የሚል ጠንካራ በሴቶች መልዕክት ተላለፏል::

የመድረክ አስተዋዋቂዋ ወ/ሮ ላቀች ደገፋ ታዳሚው ያለምንም ፍርሃትና ገደብ የመሰለውን ጥያቄ መጠየቅ እንደሚቻል ገልፀው ይሄን እንዲያስተናግድ አቶ አበባየሁ ደሜን ጋብዘው ከመድረክ ወረዱ:: ከተሰነዘሩት ጥያቄዎች መካከል ጥቂቶቹን ለአንባቢዎች ላድርስ፡-

- በምርጫ 97 ላይ . . . ኢህአዴግ ስልጣን አለቀቀም:: 2002 ምርጫ ላይ ፍትሃዊ ይሆናል ብላችሁ ታስባላችሁ?
- እንደ ቅንጅት እንደማትከፋፈሉ ምን ዋስትና አለን? ወደ ውህደትስ ለምን አታመሩም?
- ለአካል ጉዳተኞች ምን አስባችኋል? ብርቱካንን ቀዳሚ አድርጉ
- ገዥው ፓርቲ ሁሉንም ሚዲያዎች አፍኖ በያዙበት ወቅት ምን አይነት የሚዲያ ስትራቴጂ አላችሁ?
- አዳዲስ አባላትን ምን ያህል አፍርታችኋል? ብዙ ብርቱካኖች መፍጠር አለባችሁ . . . የሚሉ ነበሩ::

ለቀረቡት በርካታ ጥያቄዎች የመድረክ ሊ/መንበር የሆኑት ዶ/ር መረራ ጉዲና መልስ የሰጡ ሲሆን «ኢህአዴግ በፍትሃዊ ምርጫ ያምናል ወይ? በአሁኑ ምርጫ እንኳን ከ200 ሺ በላይ ታዛቢዎች የኢህአዴግ አባልና ደጋፊዎች መሆናቸውን እናውቃለን:: እሱ ተወዳዳሪ ዳኛም የሆነበት ምርጫ ነው:: የምርጫ ታዛቢዎች ፍትዊና ነፃ ካልሆኑ እንዴት ነፃ ምርጫ ሊካሄድ ይችላል? ኢህአዴግ ባንድ እጁ ጠብመንጃ በሌላ እጁ የምርጫ ሳጥን ይዞ ነው የሚወዳደረው::» የሚሉ አስተያየቶች ተሰንዝረዋል::

የብርቱካንን ጉዳይም «የብርቱካን ወንጀሏ ትልቅ ፓርቲ ለመምራት የተመረጠች የመጀመሪያ ሴት የተቃውሞ ፖለቲካ መሪ መሆንዋ ነው:: ብርቱካን የሴት ማንዴላ ነች:: መድረክ ሲያሸንፍ ነፃ ትወጣለች::» በማለት ዶ/ር መረራ መልሰዋል:: «እንደ ቅንጅት እንዳትሆኑ» ለሚለው ጥያቄ ከመድረኩ የተሰጡው ምላሽ «እኛ የልምድም ሆነ የችሎታ ችግር የለብንም:: ስለዚህ እናንተ ከደገፋችሁን እናድጋለን::» ብለዋል::

ፈተናው የናንተም ጭምር ነው:: ዋስትናችን በቁርጠኝነት ተያይዘን ትግሉን ለመቀጠል ስንችል ነው:: የአካል ጉዳተኞችን በተመለከተም «በመድረክ ፕሮግራም እንደተካተተ ጠቁመው ትግሉን ቀጥሉ በጋራ እንታገል» ሲሉ መልሰዋል::

ከዶ/ር መረራ ቀጥሎ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ፣አቶ ተመስገን ዘውዴ፣አቶ አንዱዓለም አራጌ፣አቶ ብሩ በርመጅ እና ሌሎችም በሁለት ዙር ለቀረቡ ጥያቄዎች መልስ ሰጥተዋል:: በዕለቱም ብርቱካን የታሰረችበት 14ኛ ወር ከታዳሚው ጋር ሻማ በመለኮስ ተከብሯል:: ስብሰባውም ኢትዮጵያዊ ጨዋነትን በተላበሰ መልኩ ነበር የተጠናቀቀው::

## መድረክ በአዲስ . . .

(ከገጽ 1 የዞረ)

ጠንክሩ፣ በርቱ፣ከጐናችሁ ነን በማለት ድጋፉን አሳይቷል:: በሁለቱም ስብሰባዎች ላይ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የመድረኩ ሊ/መንበር የተከበሩ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉ ሲሆን በንግግራቸውም አፅንኦት በመስጠት በኢትዮጵያ ዴሞክራሲ አለ ከተባለ በኢህአዴግ ቁመት ልክ የተሰራ የዴሞክራሲ ጥብቆ ነው ሲሉ ኢህአዴግ አሰፈንኩት ያለውን ዴሞክራሲ ተችተዋል:: በመቀጠልም መድረክ ከየት መጣ? የሚል ጥያቄ አንስተው መድረክ የመጣው የሁላችንም የምትሆን ኢትዮጵያን ለመፍጠር ከተሰባሰቡ ኃይሎች ነው በማለት ዶ/ር መረራ ጉዲና ገልፀዋል:: መድረክ 65 ገፅ ያለው መለስተኛ ፕሮግራም ይዞ እየተንቀሳቀሰ እንደሆነም ተገልፆአል:: ዶ/ር መረራ «ኢህአዴግ ለራሱ ሰላምና መረጋጋት ፈጥሮ ሊሆን ይችላል ለኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ሰላምና መረጋጋት መፍጠር አልሆነለትም» በማለት የሰላ ትችት አቅርበዋል:: በተለይም በድል በር ት/ቤት አቶ ዘካርያስ የማነብርሃን የተባሉ መምህር «ምንድን ነው ዝምታ?» የሚል ግጥም በጥዑም አነባበብ ያቀረቡት የተሰብሳቢውን ቀልብ የሳበ ነበር:::: በግጥሙም መምህሩ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የተጫነው ቀንበር የዴሞክራሲ እጦት ነውና ዝምታው ይሰበር የሚል መልዕክት አስተላልፈዋል:: ከመድረኩ አመራር አባላት መካከል የአንድነት ፓርቲ ዋና ፀሀፊ የሆኑት አቶ አንዱዓለም አራጌ ኢህአዴግ ብርቱካንን ያሰራት ፈሪ ስለሆነ ነው በማለት የታዋቂው አሜሪካዊ ዘጋቢያችን እንዳደረሰን ከሆነ ሕዝቡ የሰላም ታጋይ የሆነችውን ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ መታሰሯን አምርሮ እየተቃወመ ሲናገር እንደነበር ማስተዋሉን ገልፀዋል:: አንዳንድ አስተያየት ሰጭዎችም ወ/ት ብርቱካን በዓለማቀፍ ደረጃ እንደ በርማዋ ታጋይ ሳን.ሱኪ ስሟ ከፍ ሊል ይገባዋል ሲሉ በሁሉም ስብሰባዎች የወ/ት ብርቱካንን መታሰር ተቃውመዋል:: የጥቁሮች መብት ተሟጋች ማርቲን ሉተር ኪንግ ባለቤት በአንድ ወቅት ተጠይቀው የተናገሩትን አስታውሰዋል:: «ባለቤቴን ፈሪዎች ባንድ ጥይት ገድለውታል ነገር ግን መካዞን ውስጥ ያለውን ጥይታቸውን ሁሉ ቢጨርሱ እንኳን የያዙውን እውነት አይገድሉትም::» ብለዋል እናም አሉ አቶ አንዱዓለም የብርቱካንን ሀቅ ፈርተው ቢያስሯትም እውነቷን ማሰር አይችሉም በማለት ገልፀውታል:: ዶ/ር ኃይሉ አርዓያም በበኩላቸው የገዥውን ፓርቲ ፍርሃትና ወከባ የፈሪ በትር 12 ነው ሲሉ ገልፀዋል:: ከታዳሚው የተለያዩ ጠያቄዎች የተነሱ ሲሆን መልስም ተሰጥቶባቸዋል:: መድረክ በሁለት ቦታዎች ከአዲስ አበባ ኗሪዎች ጋር ያደረገውን ምክክርና ውይይት በተሳካ ሁኔታ አጠቃሏል::

# ሰዎች ምን ይላሉ?

# ሕዝብ በተቃዋሚዎች በተቃዋሚዎች ያለው አመኔታ ምን ያህል ነው?

ዳሰሳ ከዩሐንስ ተክሉና መንገሻ ክሉ

በጉራጌ ዞን እነሞርና ኤነር ወረዳ ላይ ያለው የኢህአዴግ መዋቅር በሌሎቹ አስራ ሁለት የጉራጌ ወረዳዎች ካለው መዋቅር የጠነከረ ነው ተብሎ ቢታወንመ በወረዳው ከላይ እስከ ታች ያለው የመንግሥት አስተዳደር ግን ኢህአዴግ የሚታወቅበትን በይፋ ሕግን የመጣስና ማን አለብኝነት ባህሪ በዞኑና በወረዳው ለመተግበር የሚያስችለ ጨለም ሕሊና ያላቸው:: በመኑም ይህ ወረዳ ኢህአዴግ በከፍተኛ ጥርጣሬ ከሚያ ያቸው አካባቢዎች ሊመደብ ይችላል:: ለዚህም ምሣሌ ከሚሆኑን ጉዳዮችና ክስተቶች ኢህአዴግ በስለጣን ላይ ካስቀመጣቸው ባለሥልጣናቱ ከሕብረተሠቡ ጋር በተለያዩ ማሕበራዊ ጉዳዮች የተሣሠሩ በከፊልም ለውጥ ፈላጊዎችና ለሕብረተሠቡ መልካም ባሕላዊ ስሌቶች የተገዙ መሆናቸው እናም ለአብላጫው ሕዝብ ፍላጐት በስውርም ቢሆን ይተ ባበራሉ::

በምርጫ ዘጠና ሰባት ቅንጅት በእነሞር ቁጥር ሁለት የምርጫ ክልል ላይ ዕጩ አልነበረውም:: ነገር ግን በወረዳው የመንግሥት አስተዳደር ውስጥ ያሉ ጥቂት ስዎች «ለምንድነው በገወዳችን ቅንጅት ተወዳዳሪ ያላስመዘገበው» በሚል ተነጋግረው በራሣቸው መንገድ አንድ ጠንከራ ዕጩ መርጠው በማነጋገር እንዲመዘገብ አድርገው ያም ዕጩ አሸንፎ ፓርላማ መግባት ችሏል:: እኛም በተወላጅነታችን ከአዲስ አበባ ለመመዝገብ ከመሄዳችን በፊት የተቃዋሚ ዕጩ በምርጫ ክልሉ የለም እንዳይባል ብቻ ማንንም ቢሆን ለማነጋገር ፊልገው እንደ ነበር ነግረውናል::

በዕጩነት ለመመዝገብ በሄድንበት ወቅት ይገጥመናል ብለን ፈርተነው በነበረው በኢህአዴግ መሠሪ ባህርይ በብሔሩ መልካም የተለመደ ከብርና ትህትና ነበር የተቀበሉን::

በምርጫ ዘጠና ሠባት ቅድመ ምርጫና ድህረ ምርጫ በጣም ጥሩ ነበር:: ለዚህም ከሚጠቀሱ ምክንያቶች የሕዝቡን መሠረታዊ ፍላጐቶች የፖለቲካ ፕሮግራም ያላቸው ፓርቲዎች ይህንን በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ ግንባር ቀደም ሚና እየተ ጫወተ ያለና በሁሉም የኢትዮጵያ ብሔረ-ሰቦች ዘንድ የአብሮ መኖርና የአንድነት ምሣሌ የሆነውን ሕዝብ ከኋላቸው ማስከተል ይችላሉ::

በምርጫ ዘጠና ሠባት ጉራጌ የምርጫውን ሚዛን ወደ አንድ አቅጣጫ እንዲህ አይነት ግንባር ቀደም ሚና እንዲጫወት በሕዝቡ ላይ የከፋ የበቀል በትሩን አንስቶበት ነበር:: በመቀጠልም ሕዝቡን ለማግባባት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል:: ከጥረቶቹም የብሔሩን አባላት ፊት ለፊት ማነጋገርና እስከ ዞኑ ድረስ በመሄድ ለዩኒቨርስቲ ግንባታ የመሠረት ድንጋይ ማኖር ይጠቀሣሉ:: በዚህም ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአካል ለዞናዊ ጉዳይ በመውረደቸው አንዳንዶች «መለስ ዜናዊ በኦዮ ስቴት ለዩኒቨርስቲ ግንባታ የመሠረት ድንጋይ አኖሩ!» ሲሉ የሕዝቡን የኢትዮጵያ ምርጫ ውጤት ወሣኝነትን በቀልድ የአሜሪካዋን የኦሀዮ ስቴት ሕዝብን ከጉራጌ ሕዝብ ጋር በማነፃፀር ገልፀዋል::

የወረዳው ሕዝብ ወቅታዊ የፖለቲካ ሁኔታና ፍላጐት ለመዳሠስ አራት ጥያቄዎችን ለይተን አወያይ በሆነ መንገድ የፖለቲካ ሁኔታውን ለመረዳት ተጠቅመናል::

ጥያቄቹም:-

1. ዛሬ ኢህአዴግ ሕዝቡን ምን ያህል ተ ቆጣጥሮታል?
2. ሕዝቡ በተቃዋሚዎች ላይ ያለው አመኔታ ምን ያህል ነው?
3. ሕዝቡ አሁን ያለው የፖለቲካ ምርጫ ተነሣሽነት ምን ያህል ነው?
4. ተቃዋሚዎች ሊከተሉዋቸው የሚገቡዋቸው የምርጫ ቅስቀሣ መንገዶች ምን ምን መሆን አለባቸው? የሚሉ ናቸው::

## 1 ዛሬ ኢህአዴግ ሕዝቡን ምን ያህል ተ ቆጣጥሮታል?

ከዘጠና ሠባቱ ምርጫ በኋላ ኢህአደግ በየትኛውም መንገድ ከፍተኛ ቁጥር ያለውን ሕዝብ በግዴታም ይሁን በውዴታ የፓርቲው አባል እንደሆን በማድረጉ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ለውጥ ፈላጊው ሕዝብ ኢህአዴግን ከሥልጣን የማንሣት ጉዳይ ተስፋ አስቆራጭ ሆኖ ታይቷቸዋል:: ኢህአዴግ ከዚህ ዘመቻው ትርፍ አያገኝም ባይባልም የአባላት ምልመላው ሁኔታ የብዘ ኢትዮጵያዊያንን ዴሞክራሲያዊ መብቶች የተጋፋ በመሆኑ በብዙዎቹ ዘንድ በተለይም በተማረው ክፍል ከፍተኛ የሆነ መማረርና ጥላቻን ፈጥሮአል::

ከምክንያቶቹም ዜጐች በጐነታቸው ሊያገኙዋቸው የሚገቡዋቸውን መብቶች በመግፈፍ የዜጐች የመስራት የመማርና የመንቀሣቀስ መብቶች በዜግነታቸው ሣይሆን በኢህአዴግ አባልነታቸው ብቻ የሚከበርላቸው በመሆኑና ለሕብረተሠቡ መሠረታዊ ጠያቄዎች በቀጥታ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ በፈቀደው መንገድ ብቻ ሕዝቡን የመንዳት ፍላጐቱ በጥቂቱ ናቸው::

ይህም ሆኖ ኢህአዴግ በጉራጌ ዞን በእነሞርና ኤነር ወረዳ ዜጐችን አባል የማድረግ ስራው ደካማ ነው ለማለት አንችልም:: ከላይ እንደተገለፀው ኢህአዴግ በወ ረዳው የአባላቱን ቁጥር ለማብዛት በሄደበት ሂደት አዳዲስ አባላተን ብቻ ሣይሆን ያገኘው ዜጋ ሁሉ የፓርቲያችን አባል ካልሆናችሁ ስራ አታገኙም የመማርም ዕድልም አይኖራችሁም በመባላቸው ከፍተኛ ቅሬታንም ፈጥሮአል:: በመሆኑ ሕዝቡ ሀገሪቷን የሚ ረከብ ጠካራ ፓርቲ አለወይ? የሚለውን ጥያቄ የጠየቁን::

**<u>በእርግጥ አሁን ሕዝቡን ከኢህአዴግ እስራት ነፃ የሚያወጣ ጠንካራ ተ ቃዋሚ ፓርቲ አለወይ? ኢህአዴግ ሕዝቡን የመቅጠሩንና ያለመቅጠሩን ጉዳይ ከላይ ላቀረበው ጥያቄ ለሚሠጠው ምላሽ ይወሠናል::</u>**

## 2 ሕዝቡ በተቃዋሚዎች ላይ ያለው አመኔታ ምን ያህል ነው?

በዘጠና ሠባቱ የምርጫ ሂደት በዞኑ ብሎም የእነሞርና የኤነር ወረዳ ነዋሪዎች ይህንን ያህል ነው ተብሎ ሊገለፅ በማይችል መጠን በተቃዋሚዎ ላይ እጅግ ከፍተኛ የሆነ አመኔታ ነበራቸው::

ሕዝቡ ደርሶብኛል በሚላቸው ልዩ ልዩ በደሎችና መሠላቸት ምክንያት ከኢህአዴግ አገዛዝ ነፃ የመውጣት ፍላጐቱ እጅግ ንሮ ነበር:: የምርጫውን መጠናቀቅ ተ ከትለው የተከሠቱ በርካን ተስፋ አስቆራጭ ከስተቶችን የኢህአዴግ ባለስልጣን መቀጠል ብሎም ተስፋውን የጣለባቸው የተቃዋሚ መሪዎች በሠሩት ታሪካዊ ስህተት የሕዝቡን ተስፋ እንደ ጧት ጤዛ አርግፈውታል:: ከላይ የተጠቀሠውን ጥያቄ በተመለከተ በአሁኑ ወቅት የወረዳው ነዋሪ እንደየትኛውንም ኢትዮጵያዊ ሁሉ ጠንካራ የተ ቃዋሚ ፓርቲ ከመጣ ድጋፍ የመስጠት ፍላጐት ይታይበታል:: ሆኖም ሕዝቡ ከዘጠና ሠባቱ ምርጫ በተ ለይም ከተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች መበታተን የተማረው የተቃዋሚ ፓርቲዎች ውስጣዊ አደረጃጀታቸውና ቀጣይ ሂደቶቻቸው ምን ዓይነት ገፅታ እንዳለው መለየትን ነው::

እና በአሁኑ ወቅት ይህ ነው የሚባል የተቃዋሚዎች እንቅስቃሴ ሳይታይ የወረዳው ነዋሪዎች ላይ ይህንን ያህል እምነት አላቸው ለማለት የሚያስደፍር ሁኔታ የለም:: ነገር ግን ጠንካራ ተቃዋሚ ፓርቲ ኖረም አልኖረ አብዛኛ ው ሕዝብና ኢህአዴግ ዛሬም ሆድና ጀርባ ናቸው::

ለዚህም እውነታ ማሣያ ከሚሆኑን ነገሮችና ሁለቱ ሕዝቡ ዝሮም ከቅንጅት ትውስታ ያልተላቀቀ መሆኑና ቀበሌ ሄዶ የምርጫ ካርድ አለመውሠዱ ይጠቀሣሉ::3

## <u>3. ሕዝቡ ዛሬ ለፖለቲካ ምርጫ ያለው ተነሳሽነት ምን ያህል ነው?</u>

ሕዝቡ ከዘጠና ሠባቱ ትዝታው ተላቆ አሁን ስላለው ምርጨ የማሠብም ሆነ ዝንባሌ አይተነበይም ለአብዛኛው የወረዳው ነዋሪ ከዘጠና ሠባቱ ምርጫ ወዲህ ስለሌለ ምርጫ ማውራት አይሆንለትም ምክንያት የምርጫው ጠቅላላ ሂደት በኢህአዴግ እጅ የወደቀ ነው ብሎ ማመኑ ነው:: ከዚህ አብይ ተቃዋሚዎች ሠፊ የሆነ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች መስራት ይኖርባቸዋል:: በዳሰሳችን ወቅት ስለ ምርጫ ስናነሳለት ያለን ነገር የብዜውን ሕዝብ አስተሣሠብ ጠቅልሎ የያዘ መሆኑን ተረድተናል:: ያለችን «ራሣቸው ምርጫውን መርጠው ጨርሠው ይመጣና እኛ ን ለመታዘብ ምርጡ ይሉናል» ነበር::

እንደ ሁሉም የኢትዮጵያ አካባቢዎች ሁሉ በዚሁም ወረዳ ሕዝቡ የምርጫ ካርድ መውሠድ ምን ያደርግልናል በሚል ዕሣቤ:: እናም ተቃዋሚዎች ሚዲያዎች ከሚያገኙት ሽፋንና ሕብረተሠቡ ውስጥ በአካል ተገብቶ በሚሠራው የቅስቀሣ ስራ የሕዝቡን የምምረጥ ተነሣሽነት ከፍ ከማድረግ ይቻላል ብለን እናምናለን::

# ምርጫችሁ በእጃችሁ ነው!!



## የመድረክ የምርጫ ፍቺ

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ አንድነት መድረክ መድረክ የ8 የፖለቲካ ድርጅቶች ጥምረት ፓርቲ ነው:: የ2002 ዓ.ም የምርጫ ምልክቱ የእጅ መዳፍ ሲሆን መድረኩ ይህንን ምልክት የመረጠበት ምክንያት የሰላም የፍቅር የአንድነት የብሩህ ተስፋ ምልክት በመሆኑ የመላው የኢትዮጵያን ሕዝብ ፍላጎትና እምነት የሚያሟላ መሆኑን በማመን ነው:: ስለዚህ መድረክን ምርጡ!! ኢትዮጵያን የበለፀገችና ሰላም የሰፈነባት ሀገር ለማድረግ የተሟላ ዝግጅት አድርገናል::**

# መድረክን ምረጡ እንዳትበለጡ ነፃነታችን በእጃችን

## የጉራጌ ዞን

ከገፅ 4 የዞረ

በሕገ መንግሥታችን የዜጐች እኩልነት ተዘዋውሮ የመማር መብት የተረጋገጠ ቢሆንም የኢህአዴግ ፌዴራላዊ አስተዳደር ግን በተግባር ሲታይ የዜጐችን በመላው ኢትዮጵያ ተዘዋውሮ የመኖር የመስራትና የመማር መብታቸው አደጋ ውስጥ ከገባና ብሔራዊ ቁርሾ ከፈጠረ ቆይቷል::

ከዘጠና ዘባቱ ምርጫ በኋላ በዚህ ርዕሠ ጉዳይ ውስጥ ሊካተቱ የማያስፈልጉ ከፍተኛ በደሎችን ግድያዎች በከተሞች በሚኖሩ የብሔረሰቡ አባላት ላይ ተፈፅሟል::

በናዝሬት ከተማ የሚኖሩ የብሔረ-ሠቡን አባላት ባነጋገርንበት ወቅት የኢህአዴግ የፖለቲካ ስርዓት የፈጠረባቸውን ከፍተኛ ጫና በቀላሉ መግለፅ እንደማይችሉ በምሬት ተናግረዋል:: የብሔረሠቡ አባላት በከተማው ውስጥ የመኖርና የመስራት ፍላጐታቸው በጣም ቀዝቃዛ ነው በመሆኑም የፖለቲካው ስርዓት ምንም ዋስትና ስለማይሠጣቸው ሁሉም የብሔረሠቡ ባለሀብቶች በከተማዋ ወስጥ ተንቀሣቃሽ እንጂ ቋሚ ሀብት አያፈሩም:: ይሄ ደግሞ የጠቅላላውን የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ምን ያህል እንደሚከዘጠና ሰባቱ ምርጫ በኋላ እንደመርካቶ ሁሉ በናዝሬት ከተማ ውስጥ በጉራጌ ብሔር አባላት ይመራ የነበረውን ትልቅ የገበያ ማዕከል የክልሉ አስተዳደር በማይረባ ምክንያት የብሔረሠቡን አባላት ከገበያ ቦታው ለማፈናቀል በወሰነው ውሣኔ ሕዝቡ ለከፍተኛ ችግር ሲጋለጥ ይህንን በደል ከተቃወሙ በርካታ ሠዎች መካከል ወደ ሣያ የሚጠጉት በፖሊስ ተገድለዋል::

ሕዝቡ ለዚህ ሁሉ ችግር ያጋለጠው የኢህአዴግ ከፋፍሎ የማናቆርና የመግዛት ፖለቲካ መሆኑን በደንብ ስለሚያውቅ ብሔሩ የራሱንም ሆነ የሌሎች ኢትዮጵያውያንንመሠረታዊ ባህሪያት ያገናዘበ የፖለቲካ ስርዓት እንዲዘረጋ ፅኑ ፍላጐት አላቸው::

እንዲሁም የብሔረሠቡ አባላት በባህሪያቸው ለነፃ አስተሳሰብና ለሕብረ-ብሔራዊነት በጣም የቀረቡ በመሆናቸው የሊብራል ዴሞክራሲ ስርዓትን ምንነት በይበልጥ በማስረዳትና ሕዝቡ ምንም ሣይሸማቀቅና ሣይፈራ በብሔር ሣይከፋፈል በኢትዮጵያዊነቱ በእኩልት በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች መኖር መስራትና መማር የሚያስችለውን የፖለቲካ ስርዓት እንዲዘረጋ ከተጠየቀ ድምፁን ከመስጠት ወደ ኋላ አይልም::

በመሆኑም በግለሠብ መብት ላይ የተመሠረተውን የሊብራል ዴመክራሲ ስርዓት ከማንም ከላይ የጉራጌ ብሔር አባላት ይናፍቁታል:: አንደኛ ይህ የፖለቲካ ስርዓት ኢትዮጵያውያንን በብሔር ሣይሆን በኢትዮጵያዊነታቸው ስለሚያስተሣስራቸው ሁለተኛ የጉራጌ ብሔር አባላት በሁሉም የኢትዮጵያ ክልሎች ከየትኛውም ዜጋ እኩል የመኖር የመስራትና የመኖር መብት ስለሚያጐናፅፋቸው እናም የዴሞክራሲና የዜጐች እኩልነት ጉዳይ ከማንም በላይ ለጉራጌ ሕዝብ እጅግ አንገብጋቢ ጉዳይ በመሆኑ ተ ቃዋሚ ፓርቲዎች የብሔረሠቡን ይሁንታ ለማግኘት በዚህ ረገድ ጠንክረው በዘላቂነት ከሠሩ ቀላል ይሆንላቸዋል::

### 2.የግብርናው ገፅታ

ኢህአዴግ የሚያራምደው ግብርና መር የኢኮኖሚ ስርዓት የሚያስገኘው ጠቀሜታ በተለያዩ አካባቢዎች በአዝጋሚ ሂደት በጥቂቱ ለውጥ ቢታይም በጉራጌ ዞን ግን የኢህአዴግ የግብርና ፖሊሲ ሽባ ሆኗል:: ለዚህም በተለይ የሚቀርበው

ምክንያት ባለው ጠባብ መሬት ላይ ብዘ ምርት ለማግኘት የሚያስችሉ የግብርና ግብአቶችና ምርታማ የሚያደርግ የማማከር አገልግሎት ሕዝቡ የሚያገኝ አለመሆኑ ነው::

እኛም ግብርናውን በተመለከተ ያነጋገርናቸው ጥቂት ገበሬዎች ሕይወታቸውን መለወጥ የሚችል ውጤት እንደማያገኙና ይልቅ አድካሚነቱ እንደሚጐላባቸው ነግ ረውናል::አንድ ከግብርና ስራ ሲመለስ አግኝተነው ስለገብርናው ስራና የሕዝቡ የፖለቲካ ምርጫ ማን ሊሆን እንደሚችል የተመላበት ምላሽ የአብዛኛውን ጉራጌ ሐሳብ የሚያንፀባርቅ ሆኖ አግኝተነዋል:: ወጣቱም ኢህአዴግ በወ ረዳው ከሕዝቡና ከገበሬው ጋር የፈጠረውን ጥሩ ቀረቤታና እገዛ ከነገረን በኋላ «ታድያ ምርጫችሁ ኢህአዴግ ነዋ» ስንለው «ከስ ኽጃውርኩ» የሚል ምላሽ ሰጠን:: «ሆድ ይፍጀው» ማለት ነው:: ይህ ማለት ኢህአዴግ እኛን ሊያሣምን የሚያስችለውን ስራ ሣይሠራ ሠርቶልናል ብለን እንድናምን ተገደናል በአጠቃላይ የ«ሆድ ይፍጀው» ዘዮአዊ አነጋገራቸው ሐሳባቸውን በአጭሩ በደንብ ይገልጥላቸዋል:: ይህም ማለት የምንፈልገውን ሣይሆን የሚፈልጉትን ይነግሩናል:: አቅም ስለሌለን እያወቅን እንዳላወቅን ሣንገዛ እንደተገዛን ሣንስማማ እንደተስማማን ሆነን እንኖራለን የሚል ዕሣቤ ያለው ጠንካራ አባባላቸው ነው::

በመሆኑም መንግሥት «ግብርና» እያለ ቢጮህም ለግብርናው ዘርፍ ለወጥ ሊያመጣ የሚችል ትኩረት ስላልተሠጠው ተቃዋሚዎች በወረዳው ላለው የግብርና እንቅስቃሴ የግብርና ግብዓቶችን ከማቅረብ እስከ ባለሙያ እገዛ ድረስ በቅርበት እንደሚሠሩ ለሕዝቡ ቢገልፅላቸው ትኩረታቸውን ማግኘት ይችላሉ::

### ማጠቃለያ

በዞኑና በወረዳው ያለው የመንግሥት ሠራተኛው በተለይም የፖለቲካ ሠራተኛው በኢህአዴግ ፖለቲካ ዕምነት ባይኖረውም በኢህአዴግ ስልጣን መልቀቅ ምክንያት የኢኮኖሚ ተጠቃሚነቱን እንዳያጣ ከፍተኛ ስጋት ስላለበት ቤተሠቡንም ጭምር በማስተባበር ላላመንበት የፖለቲካ ስርዓት ጠበቃ የመሆን ዝንባሌ ይታይበታል:: በመሆኑም ተቃዋሚዎች ስልጣን ቢይዙ ለነዚህ ሠራተኞችና ቤተ ሠቦቻቸው የተሻለ የኢኮኖሚ ተጠቃሚ እንደሚሆኑና በነፃነት እንደሚኖሩ ቀድመው ሊያረጋግጡላቸው ይገባል::

በማጠቃለያችን ኢህአዴግን በአጭር ጊዜም ሆነ በረጅም የጊዜ ሂደት በምርጫ ከስልጣን ለማስነሣትና ኢትዮጵያ እንዲኖራት የምትፈልገውን የፖለቲካ ማሕበረሠብ ለመፍጠር ሦስት ነገሮች እጅግ ወሣኝ መሆናቸውን ተረድተናል:: እነዚህም

1. ሕዝባዊ የሆኑ የፖለቲካ ርዕዮት
2. ጠንካራ መሪዎችና መዋቅር
3. ገንዘብ ናቸው::